# የኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኅበር

# የተሻሻለ መተዳደሪያ ደንብን

ሚያዚያ **5/2011** ዓ.ም

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ግንቦታ ለማፋጠን ትምህርት የሚጫወተው ሚና ወሳኝ መሆኑ ግልፅ ነው፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ባለፉት ሁለት አስርት ዓመታት የሀገሪቱ የትምህርት እና የኢንቨስትመንት ፖሊሲ በፈጠረው ዕድል በመጠቀም የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት በከፍተኛ ፍጥነት ያደጉ ሲሆን በዘርፉ ነባር ዕድሜ ባላቸው ተቋማት አነሳሽነት በማኅበር የመደራጀት እና ዘርፉን አስተባብሮ የመምራት አስፈላጊነት በመታመኑ በ**1995** ዓ.ም. በአዲስ አበባ ንግድ ምክር ቤት ጥላ ስር በመደራጀት ጥቂት ተቋማት የጋራ እንቅስቃሴ ማድረግ ጀመሩ፡፡ ይህንን በአዲስ አበባ ብቻ የተገደበ እንቅስቃሴና አደረጃጀት በመላው ሀገሪቷ ለማስፋፋት ፍላጎቱ የነበረ ቢሆንም ብዙዎቹ  ተቋማት የትርፍ በማህበራት አደረጃጀት ስለነበራቸው የጋራ ማህበሩን ለማስመዝገብ የተደረገው ጥረት ብዙዎቹ ተቋማት የትርፍ በማህበራት አደረጃጀት ስለነበራቸው የጋራ ማህበሩን ለማስመዝገብ የተደረገው ጥረት በፍትሕ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በኩል ለተወሰኑ ጊዜያት ተቀባይት ሣያገኝ ቆይቷል፡፡ ሆኖም በውቅቱ የነበሩት የትምህርት ሚኒስቴር ከፍተኛ ኃላፊዎች የማህበሩን መመስረት አስፈላጊነት ከፍትህ ሚኒስቴር ጋር ባደረጉት ምክክር ማህበሩ በ**12** (አስራ ሁለት) መሥራች ተቋማት ሚያዚያ **22** ቀን **1996** ዓ.ም. በሕጋዊነት ለሚሠረት ችሏል፡፡

በወቅቱ የነበረው የመተዳደሪያ ደንብ መሻሻል ባስፈለገባቸው ጊዜያቶች ማለትም በ**1998**፣ ዓ.ም. በነሃሴ **1999**፣ በጥር **2001**፣ እና በ**2005** እንዲሻሻል ተደርጓል፡፡

ማህበሩ ከዚህ በፊት ሲቋቋም በበጎ አድርጎት ማህበራት ማደራጃ ፅንሰ ሃሳብ የተቋቋመ ቢሆንም በአሁኑ ወቅት የማህበራት ማደራጃ በግልፅ ባስቀመጠው መሰረት እንደዚህ አይነት ማህበር ሊያቅፍበት የሚችል የህግ ማዕቀፍ ባለመኖሩ ምክንያት ማህበሩ እንደገና በኢትዮጵያ ንግድ ሚንስትር ስር በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር **980/2008** መሰረት ና በንግድ የዘርፍ ማህበራት መደራጀት እንዳለበት ይደነግጋል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር **392/2009** መሰረት የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት በማውጣት መንቀሳሰቅ እንዳለበት በመወሰኑ ምክንያት ማህበሩ ከላይ የተገለፁትን አዋጅ እና ደንብ ቁጥር ባገናዘበ መልኩ የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብም በድጋሚ መሻሻል አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በዚህም መሰረት ይህ መተዳደሪ ደንብ ከላይ የተጠቀሱትን አዋጅ እና ደንብ መሰረት በማድረግ እንደገና ተዘጋጅቷል፡፡

**በአጠቃላይ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በወንድ ፆታ □ተቶለና**ው በሙሉ ለሴት ፆታም የሚያገልግል ይሆናል፡፡

# አንቀጽ አንድ

## ስያሜ

በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የተቋቋመው ማኅበር ***የኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኅበር*** በሚል ስም ይጠራል፡፡

# አንቀጽ ሁለት

## ትርጉም

**6.1 ማኅበር** ማለት በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ለትርፍ ያልተቋቋመው የኢትዮጵያ የግል ከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማት ማኅበር ነው::

**6.2 አባል** ማለት በሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ህጋዊ ፈቃድና እውቅና አግኝቶ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ወይም/እና በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ የተሰማራ እንዲሁም ይህን መተዳደሪያ ደንብ ተቀብሎ የማህበሩ አካል የሆነ ማለት ነው::

**6.3 የንግድ እና የዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት** ማለት በአዋጅ ቁጥር **980/2008** በተጠቀሰው መሰረት ነጋዴዎች የጋራ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ በየደረጃ በሀገሪቱ ህግ መሰረት የሚቋቋሙት ምክር ቤት ነው::

**6.4 የዘርፍ ማህበር** ማለት በአዋጅ ቁጥር **980/2008** በተጠቀሰው መሰረት በአምራችነት ወይም በአገልግሎት ዘርፍ ላይ የተሰማሩ ነጋዴዎችን ወይም ያታን መሰረት በማድረግ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ንግድን ለመደገፍ የተደራጁ ማህበራት ናቸው::

**6.5 የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት** ማላት በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር **392/2009** ክፍል አንድ ተራ ቁጥር **16** መሰረት የዘርፍ ማህበራት የንግድ ምዝገባ ምስክር ወረቀት ለማውጣት ከሚቀርቡ ማመልከቻ ቅፅ ጋር መረጃዎች ተያይዘው መቅረብ የሚገባቸው ሲቀርቡ የሚሰጥ የምስክር ወረቀት ማለት ነው::

**6.6 ጠቅላላ ጉባኤ** ማለት መስራች አባላትንና በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት ተቀባይነት ያገኙ ሌሎች አባላትን ያቀፈ የማኅበሩ የበላይ አካል ነው::

**6.7 ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና** ማለት በሃገሪቱ የትምህርትና ስልጠና ፖሊሲ መሰረት በማንኛውም የሙያ ዘርፍ ደረጃቸው ከከፍተኛ ትምህርት በታች እና ከሁለተኛ ደረጃ ትምህርት በላይ በመደበኛ በኩል የሚሰጥ የትምህርት ዘርፍ ነው::

**6.8 የግል ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት** ማለት በአንቀፅ **6.7** መሰረት ትምህርት ለመስጠት የተሰማራ ባለቤትነቱ የመንግስት ወይም የህዝብ ያልሆነ ለበጎ አድራጎት ያልተሰማራ ለትርፍ የተቋቋመ ተቋም ማለት ነው::

**6.9 ከፍተኛ ትምህርት** ማለት በስነ ጥበብ፣ ማህበራዊ ሳይንስ እና በሳይንስና ቴክኖሎጂ መስኮች በቅድመ ምረቃ እና ድህረ ምረቃ የድግሪ ፕሮግራሞች በአዋጅ ቁጥር **650/2001** አንቀፅ **19** ስር በተመለከቱት የትምህርት አግባቦች የሚሰጥ ትምህርት ነው::

**6.10.የግል ከፍተኛ ትምህርት ተቋም** ማለት በከፍተኛ ትምህርት አዋጅ መሰረት በአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ በላይ ቁጥር ባላቸው ሰዎች ባለቤትነት ወይም አላማቸው ለትርፍ ባልሆነማህበራት ወይም በህብረት ስራ ማህበራት ወይም በንግድ ማህበርነት የተመሰረተ ወይም በውጭ ሃገር የተመሰረተ እና በኢትዮጵያ ውስጥ የሚንቀሳቀስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ነው::

## አንቀጽ ሦስት

## የተፈፃሚነት ወሰን

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በቴ/ሙ/ት/ስልጠና እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ ህጋዊ ፈቃድና እውቅና አግኝተው በተሰማሩ እና የማህበሩ አባል በሆኑ ላይ ተፈፃሚነት ይኖረዋል፡፡

## አንቀፅ አራት

## መቋቋም

ማኀበሩ በ**1952** ዓ.ም በወጣው የኢትዮጵያ ፍትሐብሔር ሕግ ቁጥር **404**፣ በማኀበራት ምዝገባ ደንብ ቁጥር **321/1959** እና በአዋጅ ቁጥር **621/2009** መሠረት **ሚያዚያ 22 ቀን 1996** ዓ.ም ላልተወሰነ ጊዜ ተቋቁሞ ነበር፡፡ በመቀጠል ማህበሩ በበጎ አድራጎት እና ማህበራት ማደራጃ ኤጀንሲ ተመዝግቦ ሲንቀሳቀስ የቆየ ቢሆንም የበጎ አድራጎት ድርጅት ባደረገው ማሻሻያ መሰረት ማህበሩ በድጋሜ በንግድ ምዝገባና ፈቃድ አዋጅ ቁጥር **980/2008** እንዲሁም በሚንስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር **392/2009** መሰረት በንግድ ሚንስትር ስር በንግድ ዘርፍ ማህበራት በድጋሜ **18/3/2007** ዓ.ም ተደራጅቷል፡፡

## አንቀጽ አምስት

## የማህበሩ ዓላማዎች

**4.1** የአባል ተቋማትን መብትና ጥቅም ማስከበር፡፡

**4.2** በሀገሪቱ ውስጥ የግል ከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት እንዲስፋፉ ማበረታታት፡፡

**4.3** ለአባል ተቋማት መጠናከርና ዕድገት ተገቢውን ሁሉ መፈፀም፡፡

**4.4** በግል ከፍተኛ ትምህርት □**እና የቴ/ሙ/ት/ሥ/** ተቋማትና እንዲሁም መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ የከፍተኛ ትምህርት እና ሌሎች አግባብነት ባላቸው ተቋማት መካከል ግንኙነት መመሥረት፡፡

**4.5** አባል ተቋማት ሃሳባቸውን የሚለዋወጡበትን መድረክ ማመቻቸት፡፡

**4.6** በከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና **ሙ□ ትምህርትና** ሥልጠና ዙሪያ የሚካሄዱ **ኮንፈረንሶች ሴሚናሮችና □ምርምር ስራዎች ማካሄድ፣ ማሰባሰብ፣** ማሳተም እና ማሰራጨት ፡፡

**4.7** አባል ተቋማት በጋራ ሊጠቀሙበት የሚችሉበትን የመረጃ፣ የግብዓትና የትምህርት መርጃ መሳሪያዎችን በጋራ ሊጠቀሙባቸው እና ሊያመርቱት የሚችሉበትን መንገድ ማመቻቸት፡፡

**4.8** ተከታታይነት ያለው የከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማትን ዕድገትንና የትምህርት ጥራት እንዲረጋገጥ ጥረት ማድረግ፡፡

**4.9 በከፍተኛ ትምህርት** እና **ቴክኒክና ሙያ** ትምህርት እና ሥልጠና **ተቋማት** አካዳሚያዊ ያልሆኑ ዘርፎች **የሚዳብርበትን ሁኔታ□ ማመቻቸት** ፡፡

**4.10** ተመሳሳይ አቋም ካላቸው የትምህርት፣ ሕዝባዊና ሌሎች ተመሳሳይ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር ትብብር መመሥረት፡፡

**4.11** **በግል ከፍተኛ ትምህርት** እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርት እና ሥልጠና ተቋማት ውስጥ ተገቢው ሥነምግባርና የተጠያቂነት መንፈስ የበኩሉን ድርሻ መጫወት፡፡

**4.12** ዘርፉን በመወከል በፖሊሲ፣ ስትራጂዎች፣ አዋጆች፣ ፕሮግራሞች፣ መመሪያዎችቷ ቀረፃና አፈፃፀም ላይ የበኩሉን ድርሻ መጫወት፡፡

**4.13** ማኀበሩ መረጃን ከሚያሰራጭባቸውና ከሚይዝባቸው መንገዶች አንዱ የሆነውን ኢንፎርሜሽን ኮሚዩኒኬሽን ቴክኖሎጂን ማስፋፋትና መደገፍ፡፡

**4.14** ማኀበሩ ከሀገር ውስጥና ከውጪ ለጋሽ ድርጅቶች የቴክኒክ፣ የሥልጠና፣ የገንዘብና የቁሳቁስ ድጋፍ የሚያገኝበትን መንገድ ማፈላለግ፣ ድጋፉንም መቀበልና ለሚመለከተው ማስተላለፍ፡፡

**4.15** ሌሎች ከማኀበሩ ዓላማ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ሌሎች ተግባራት ማከናወን፡፡

**4.16** ማህበሩ ለትርፍ ያልተቋቋመ የትምህርት ስርዓቱን ለማሳለጥ በግል ከፍተኛ ትምህርት እና ቴክኒክና ሙያ ተቋማት እና በመንግስት መካከል ያለውን እንደ ድልድይ ሆኖ ማገልገል ነው፡፡

**4.17** ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎት አግባብነትን እና ጥራትን ጠብቆ እንዲሄድና ተቋማት በተሰማሩበት ዘርፍ ውጤታማ እንዲሆኑ የልምድ ልውውጥ፣ ስልጠና እና የቴክኒክ ድጋፍ በብቁ ባለሙያውች ድጋፍ መስጠት፡፡

## አንቀጽ ስድስት

## የበጀት ዓመት

**5.1** የማኀበሩ የበጀት ዓመት □**እንደ ኢትዮጵያ አቆጣጠር** ከሐምሌ **01** ቀን እስከ ሰኔ **30** ቀን ይሆናል፡፡

## አንቀጽ ሰባት

## መደበኛ አባላት

***መደበኛ አባላት የሚባሉት፣***

ሀ. በማህበሩ አላማና ግብ የሚያምን፡፡

ለ. በከፍተኛ ትምህርት፤ በቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ወይም በሁለቱም ዘርፍ የተሠማራ፡፡

ሐ. የማኀበሩን የመተዳደሪያ ደንብ እንዲሁም በጠቅላላ ጉባዔው በየጊዜው የሚወጡ የሥነ ምግባር ደንቦችን የሚቀበል እና ተግባራዊ የሚያደርግ፡፡

መ. በአባላት ጠቅላላ ጉባዔ በየጊዜው ስምምነት የሚደረግባቸውን ክፍያዎችና መዋጮዎች **የሚከፍል**፡፡

ሠ. በሕግ መብቱ ያልተገፈፈ ነው፡፡

## አንቀጽ ስምንት

## የክብር አባላት

***የክብር አባላት የሚባሉት፡-***

**8.1** የማኅበሩ መደበኛ አባል ያልሆነ **ግን** የማኅበሩን አላማ ለማስፈጸም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያበረከቱ፤ ማኅበሩ በሚሰራባቸው ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማና የለውጥ አርአያ በመሆን በማኅበሩ አባላት ከፍተኛ ተቀባይነትን ያገኙ ለማህበሩ ስኬት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ የሚያደርጉ አካላት በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የክብር አባል ይሆናሉ፡፡

**8.2** የክብር አባላት በማኅበሩ ውስጥ የመምረጥ፣ የመመረጥና ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

**8.3** የክብር አባላት በራስ ተነሳሽነት የአባልነት መዋጮዎችንና ሌሎች ክፍያዎችን መክፈል ይችላሉ፡፡

**8.4** የክብር አባላት በማህበሩ ስብሰባዎች ላይ በተጋባዥነት ሊገኙ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ዘጠኝ

## የአባላት መብት

**9.1** ሁሉም መደበኛ አባላት እኩል መብት አላቸው፡፡

**9.2** የማኅበር አባልነት ለወራሾችም ሆነ ለሌላ ተቋም **አይተላለፍም**፡፡

**9.3** የማኅበሩን መሥፈርት ያሟሉ ተቋማት የማኅበሩ ሙሉ አባል ይሆናሉ፡፡

**9.4** ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ አባል፡-

ሀ. ለማኅበሩ ዓላማና ተልዕኮዎች መሳካት የሚጠቅሙ ሥራዎች የመስራት፡፡

ለ. የመምረጥ፣ የመመረጥና ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ ማንኛውንም መረጃ ጠይቆ የማግኘት፡፡

ሐ. በጠቅላላ ጉባዔው ስብሰባ የመገኘት፣ ስለማኅበሩ እንቅስቃሴ አስተያየትና ድምፅ የመስጠት፡፡

መ. ማንኛውም የማኅበሩ መደበኛ አባል አባልነቱ እንዲቋረጥ የመጨረሻ ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት በጠቅላላ ጉባኤ **ውይይት ላይ □መቆኘትና የመስማት**፡፡

ሠ. በማኅበሩ የሚዘጋጁ እና በነፃ የሚታደሉ የሕትመት ውጤቶችንና አገልግሎቶችን የማግኘት መብት አለው፡፡

ረ. አመታዊ የኦዲት ሪፖርት፣ እቅድ እና የስራ አፈፃፀም ሪፖርቶች የማግኘት መብት አላቸው፡፡

## አንቀጽ አስር

## የአባላት ግዴታ

**10.1 የአባልነት ዓመታዊ ክፍያና ሌሎች ክፍያዎችን በወቅቱ መክፈል አለበት**፡፡

**10.2** የአባልነት መዋጮውን የበጀት ዓመቱ በገባ የመጀመሪያ **ሦስት ወራት** ውስጥ ማለትም ከሃምሌ

**1** እስከ መስከረም **30** ድረስ መክፈል አለበት፡፡ በወቅቱ መዋጮ ያልከፈለ አባል ተቋም ላዘገየበት

ለዕያንዳንዱ ሩብ ዓመት የመዋጮውን **10 ኀ** በቅጣት መልክ ይከፍላል፡፡

**10.3** ማንኛውም አባል የአባላነት ግዴታውን የማይወጣ ከሆነ ከማህበሩ ሊገኙ የሚችሉ እንዲሁም

በማህበሩ በኩል የሚገኙ ሌሎች ጥቅማ ጥቅሞችን በሙሉ ማግኘት አይችልም፡፡

**10.4** አንድ አባል ከአባልነት ቢሰናበትም የሚፈለግበትን ዕዳ መክፈል ይኖርበታል፡፡

**10.5** ማንኛውም አባል የማኅበሩን የመተዳደሪያ ደንብ፣ በጠቅላላ ጉባዔ የሚወጡ መመሪያዎችና

ውሳኔዎችን ማክበር አለበት፡፡

**10.6** ማንኛውም አባል የማኅበሩን ዓላማና የገባቸውን ግዴታዎች ማክበር፣ የማኅበሩን ንብረት

የመንከባከብና የሚጠበቅበትን አገልግሎት የመስጠት ግዴታ አለበት፡፡

**10.7** በማኅበሩ መደበኛና አስቸኳይ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባዎች ላይ የመገኘት ግዴታ አለበት፡፡

**10.8** ማንኛውም አባል **የሌላውን** አባል ተቋም **መልካም** ስምና ዝና በሚያጠፋ **□ንዲሁም ጥቅም**

**□ሚያቴ** እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳታፊ መሆን አይገባውም፡፡

**10.9** ማንኛውም አባል ተቋም የሀገሪቱን ህጎች፣ የከፍተኛ ትምህርት እና የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና አዋጆች፣ ደንቦች እና መመሪያዎች የማክበር ግዴታ አለበት፡፡

## አንቀጽ አስራ አንድ

## የአባላት መዋጮና ሌሎች ክፍያዎች

**11.1** የአባልነት ዓመታዊ ክፍያ ቦርዱ ነባራዊ ሁኔታን እያየ በሚያቀርበው እና በሚያፀድቀው ይሆንና ለጊዜው ለአዲስ ገቢ የመመዝገቢያ **5=000**(አምስት ሺህ) እንዲሁም አመታዊ ክፍያው ደግሞ **5=000** (አምስት ሺህ) ብር ይሆናል ፡፡

**11.2** ማኅበሩ ሌሎች ክፍያዎች በሚኖርበት ግዜ መጠኑን እና የክፍያ ግዜውን በቦርድ ይወስናል፡፡ ተፈፃሚነቱንም ይከታተላል፡፡

**11.3** ከላይ በአንቀጽ **11** ንዑስ አንቀጽ **1** በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ የጊዜ ገደብ የማይከፍል አባል ተቋም በአንቀፅ **10** ንዑስ አንቀፅ **10.2** በገባው ውሳኔ መሰረት ተፈፃሚ ይሆነል፡፡

**11.4** አመታዊ ክፍያውን በተቀመጠው መሰረት የማይከፍሉ ተቋማት በአንቀፅ **10.3** መሰረት ለቦርድ ቀርቦ ክፍያውን የማያጠናቅቅ ከሆነ ለጠቅላላ ጉባኤ በማቅረብ ከአባልነት እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

**11.5** የአባልነት ዓመታዊ ክፍያ በተመለከተ ነባራዊ ሁኔታውን ያገናዘበ ጭማሬ ሲያስፈልገው ስራ አመራሩ አጥንቶ ሲያቀርብ በጠቅላላ ጉባዔ አብላጫ ድምፅ ሲያገኝ እና ሲወስን ሊሻሻል ይችላል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሁለት

## አባልነት ስለሚቋረጥባቸው ሁኔታዎች

**12.1** አባል የሆነው የትምህርት ተቋም ሲፈርስ፡፡

**12.2** መተዳደሪያ ደንቡ ላይ በተገለጸው መሠረት ወይም በሌላ አጥጋቢ ምክንያት ከአባልነት እንዲሰናበት

ጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን፡፡

**12.3** የማኅበሩን ክብርና ህልውና □**እንዲሁም የሌላውን አባል መልካም ስምና ዝና** በሚነካ ወይም በሚያናጋ

ተግባር ላይ መሳተፉ በማስረጃ ሲረጋገጥና ይህም በጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን፡፡

በማኅበሩ ዓላማ መሳካት በሚደረጉ እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተገቢውን ተሳትፎ ካላደረገ ወይም ለማድረግ ፍቃደኛ ሳይሆን ሲቀር እና ይኸውም በጠቅላላ ጉባዔው ሲወሰን፡፡

**12.3** □**መታዊ** መዋጮውን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ለሁለት ተከታታይ ጊዜ እስከ ስድስት ወር ድረስ ሲያዘገይ ወይም በአንቀፅ **10** ንዑስ አንቀፅ **10.2**□**እና ሌሎች ክፍያዎችን በተሰጠው የጊዜ ገደብ ባለመክፈሉ** በጠቅላላ ጉባዔው ከአባልነቱ ሲሰናበት፡፡

**12.4** ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታው ወይም መብቱን ሲነጠቅ ወይም ከአባልነት ሲወገድ፡፡

**12.5** ከማህበሩ አባልነት በራሱ ፈቃድ ለመልቀቅ በፅሁፍ ሲጠይቅና ለቦርዱ ቀርቦ በጠቅላላ ጉባኤ ሲፀድቅ፡፡

## አንቀጽ አሥራ ሶስት

## የማኅበሩ አደረጃጀት

**13.1** ማኅበሩ የሚከተሉት የአመራር አካላት ይኖሩታል፡፡

ሀ. ጠቅላላ ጉባዔ

ለ. **የሥራ** አመራር **ቦርት**

ሐ. □□·□ **ኦቲተር**

መ. **ሥራ** አስኪያጅ **(በቅዓ ር)**

**ሠ.** የጥራት ማረጋገጫ ኦፊሰር( በቅጥር)

**ረ. ሂሳብ ሹም (በቅዓ ር)**

**ሰ. ገንዘብ ያዥ (በቅዓ ር)**


**ሸ. የቢሮ አስተዳደርና የፅህፈት አገልግሎት ኦፊሰር (በቅጥር)**

**ቀ. ፅዳት □እና ተላላኪ (በቅጥር)**

በ. ሌሎች ሰራተኞች እንደአስፈላጊነቱ ይቀጠራሉ

ተ. ልዩልዩ ኮሚቴዎች(ከአባል ተቋማት የሚመረጡ)

**13.2** ማኅበሩ በሚከተለው አደረጃጀት የተዋቀረ ነው፡፡




## አንቀጽ አሥራ አራት

## የጠቅላላ ጉባኤ

የጠቅላላ ጉባዔው በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በአንቀጽ 7 መሠረት ተመዝነው ዝቅተኛውን መሥፈርት ያሟሉ ተቋማትን የሚያካትት ሆኖ በሕግና በመኅበሩ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል፡፡

**14.1** ጠቅላላ ጉባኤው የኦዲተሩንና የሥራ አመራር ቦርድ አባላትን ይሠይማል፤ የኦዲተሩንም አበል ይወስናል፡፡

**14.2** አንድ የጠቅላላ ጉበኤ ሰብሳቢ፤አንድ ም/ሰብሳቢ፤ እና አንድ ፀሐፊ ይመርጣል የአገልግሎት ዘመናቸውም አራት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም ከሁለት ጊዜ በላይ መመረጥ አይችሉም፡፡

**14.3** በማኅበሩ የፖሊሲ አቅጣጫ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ ያሻሽላል፡፡

**14.4** የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ኘሮግራም በመመርመር ዕቅድና በጀት ያጸድቃል፡፡ ያሻሽላል፡፡

**14.5** ዓመታዊ የሥራና የኦደት ሪፖርት መርምሮ ያጸድቃል፡፡ ያሻሽላል፡፡

**14.6** የማኅበሩ አባል ለመሆን በቀረቡ ጥያቄዎች ላይ ውሳኔ ይሰጣል በሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የተወሰኑ ውሳኔዎችን ያጸድቃል፡፡ ያሻሽላል፡፡

**14.7** በዚህ መተዳደሪያ ደንብ በተገለጸው መሰረት ግዴታውን ያልተወጣ አባልን ጉዳይ መርምሮ ይወስናል፡፡

**14.8** ቦርዱ የሚያቀርበውን የሥራ አፈጻጸም ሪፖርት በማድመጥ ማኅበሩ የተቋቋመበት ዓላማና የተነደፉ መርሐ ግበሮች ተግባራዊ መሆን አለመሆሃቸውን ያረጋግጣል አስፈላጊውን እርምጃ ይወስደል፡፡ ያሻሽላል፡፡

**14.9** የማኅበሩን መተደደሪያ ደንበ ያሻሽላል፡፡ በሥራ አስፈጻሚ ቦርድ የሚቀርቡ ዝርዝር የሥራ መመሪያዎችን ያጸድቃል፡፡

**14.10** የማኅበሩን ዋና መስሪያ ቤት ስለመለወጥ፤ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ስለመክፈት ይወስናል፡፡

**14.11** በማኅበሩ መፍረስ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

**14.12** ለሌላ የማኅበሩ አመራር ቦርድ ያልተሰጡ ጉደዮችን መርምሮ የወሰናል፡፡

**14.13** ጠቅላላ ጉባኤ ከመካሄዱ አስቀድሞ ባለው **15** ቀናት ውስጥ በተለያዩ ዘዴዎች ለአባላት ጥሪው እንዲደርሳቸው ይደረጋል፡፡

**14.14** ጠቅላላ ጉባኤው ሊካሄድ ወይም ሊጀመር የሚችለው ከማህበሩ አባላት ውስጥ **50፣1** ሲሟላ ጉባኤው እንዲጀመር ይደረጋል ይህም የወቅቱ የጠቅላላ ጉባኤ ሰብሳቢ ሲያረጋግጥ ብቻ ይጀመራል፡፡ ጉባኤውን ሊያስጀምር የማይችል ቁጥር ሆኖ ከተገኘ ግን ተለዋጭ ቀጠሮ ይሰጥና በሚቀጥለው በተገኘው የማህበሩ አበላት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አሥራ አምስት

## የጠቅላላ ጉባዔ ስብሰባ

**15.1** የጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባ በዓመት አንድ ጊዜ በሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አጋዥነት የሚካሄድ ሆኖ የበጀት ዓመቱ ከተዘጋ በኋላ ባሉት በሶስት ወራት ውስጥ መካሄድ ይኖርበታል፤ ሆኖም ዋናው እና ም/ሰብሳቢው ባይኖር በጠቅላላ ጉባኤ ፀኃፊ በኩል እንዲጠራ እና እንዲመራ ይደረጋል፡፡

**15.2** የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ የበጀት አመቱ ከተዘጋ ጀምሮ **እስከ 3 ወር ባለው ጊዜ ውስጥ** ስብሰባ ያልጠራ እንደሆነ በአንድ ወይም ከዚያ በላይ በሆኑ አባላት ጠያቂነት አማካኝነት በስራ አመራር ቦርድ ሰብሳቢ ወይም □ የቦርድ አባላት ጥያቄ ካቀረቡ የጠቅላላ ጉባዔውን ሰብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

**15.3** የማኅበሩ አስቸኳይ ስብሰባ በማናቸውም ጊዜ በጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ ወይም ከማህበሩ አሥር ከሙቶ የሚሆኑት በሚጠይቁበት ጊዜ ሊካሄድ ይችላል፡፡

**15.4** ለጠቅላላ ጉባዔው መደበኛ ስብሰባ አሥራ አምስት ቀናት ለአስቸኳይ ስብሰባ ደግሞ ከሰባት ቀናት

ባልበለጠ ጊዜ በፊት አባላት የስብሰባው ዝርዝር ጉዳይ፣ ቦታውን፣ ቀኑን፣ ጊዜውን እንዲያውቁት ይደረጋል፡፡

**15.5** የማኀበሩ አባላት ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

**15.6** ከላይ በአንቀጽ **16.5** የእንደተጠበቀ ሆኖ ምልዓተ ጉባዔው ስብሰባዎች ካልተሟላ የሚቀጥለው ስብሰባ በተገኙት አባላት እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስድስት

## የጠቅላላ ጉባዔው አመራር አካላት ሥልጣንና ተግባራት

***16.1 የጠቅላላ ጉባዔው ሰብሳቢ፡-***

ሀ. የጠቅላላ ጉባዔውን ስብሰባ አጀንዳ ከጸሐፊው ጋር በመሆን ይመዘግባል፡፡

አጀንዳውንም ከውይይት በፊት በጠቅላላ ጉባዔው **አቅርቦ** ያፀድቃል፡፡

ለ. የጉባዔውን ስብሰባ በሊቀመንበርነት ይመራል፡፡

ሐ. ለጉባዔው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ቅደም ተከተል በማውጣት ለውይይት እንዲቀርቡ □□**ርፉል**፡፡

**መ. ጉባኤውን ከስብሰባው 15 ቀናት በፊት ይጠራል አጀንዳውንም ይልካል**፡፡

ሠ. አስቸኳይ ጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ሲኖር ከአንድ ሳምንት በፊት /7 **ቀናት በፊት**/ **ይጠራል አጀንዳውንም** □**ልካል**፡፡

ረ. ቃለ ጉባኤ ተዘጋጅቶ ለማህበሩ ጽ/ቤት መድረሱን ያረጋግጣል፡፡

***16.2 ም/ሰብሳቢ***

ሀ. ሰብሳቢው በማይኖርበት ጊዜ ሰብሳቢውን ተክቶ ይሰራል፡፡

ለ. በሰብሳቢው የሚሰጡ ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

***16.3 ፀሐፊ***

ሀ. ከሰብሳቢው ጋር በመሆን ለጉባዔው አጀንዳዎችን ይመዘግባል፡፡

ለ. የጉባዔውን ስብሰባ ቃለ ጉባዔ ይይዛል፡፡

ሐ. ቃለ ጉባኤው በነበሩት አባላት ፊርማ ተፈርሞ በአንድ ሳምንት ውስጥ ለማህበሩ ፅ/ቤት ገቢ ያደርጋል፡፡

## አንቀጽ አስራ ሰባት

## የጠቅላላ ጉባዔ ድምፅ አሰጣጥ

**17.1** ማንኛውም አባል በጠቅላላ ጉባኤው ስብሰባ ላይ ተገኝቶ ድምፅ በሚሰጥበት ጉዳይ ላይ የሚሰጠው ድምፅ አንድ ብቻ ይሆናል፡፡

**17.2** ማንኛውም የማኅበሩ አባላት እኩል ድምፅ አላቸው፡፡

**17.3** ማንኛውም የማኅበሩ አባል ተቋም ድምፅ የሚሰጠው በተቋሙ ፕሬዚዳንት /ዲን/ ወይም እሱ በማይኖርበት ጊዜ በዚሁ ኃላፊ በጽሁፍ በሚወከል ሌላ ሰው ሊሆን ይችላል ሆኖም የተወከለው ሰው ሌላ ሰው ሊወክል አይችልም፡፡

**17.4** የድምፅ አሰጣጡ ሥነ ሥርዓት ፍትሃዊ፣ ነፃና ግልጽ በሆነ መንገድ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

**17.5** ከጠቅላላው ጉባዔ የተለየ ሃሳብ ያለው የልዩነት ሃሳቡን በቃለ ጉባዔው ላይ ለይቶ ማስፈር ይችላል፡፡

**17.6** **ውሳኔ የሚተላለፈው** በጠቅላላ ጉባኤ አባላቱ **50 ፡1 ድምጽ ይሆናል**፡፡

**17.7** የምርጫው ስርዓቶችና የመመዘኛ ነጥቦች ለአባላት በሰፊው እንዲያውቁትና ግልፅ አሰራርን እንዲይዙ አስፈላጊውን ጥረት ያደርጋል፡፡

**17.8** ምርጫው የተሟላ ለማድረግ እና በቀጣይም የተሸለ አሰራር ለመዘርጋት አመች እንዲሆን ቢቻል ከልዩ ልዩ ዘርፎች የሚጠቆሙ ዕጩ ተመራጮችንእንዲቀርቡ ይደረጋል፡፡

**17.9** ምርጫው የሚከናወነው በእለቱ በሚመረጡ **3** አስመራጭ ኮሚቴ ይሆንና የስራ ድርሻቸውን እርስ በርስ ይከፋፈላሉ፡፡ ምርጫው ከተጠናቀቀ በኋላ አስመራጭ ኮሚቴው ወድያውኑ ይፈርሳል፡፡ ሆኖም ግን የምርጫ ሁኔታውን በተመለከተ አስመራጭ ኮሚቴ የፅሁፍ ሪፖርት ለስራ አስኪያጅ ፅ/ቤት በሳምንት ውስጥ ገቢ ያደርጋሉ ፡፡

## አንቀጽ አሥራ ስምንት

## የጠቅላላ ጉባኤ የምርጫና የውሳኔ አሰጣጥ

**18.1** ማኅበሩ የሚመራው በአባላት ሙሉ ተሳትፎ በተመረጡ ሰዎች ይሆናል፡፡

**18.2** ጉባዔው ምርጫ ሲያደርግ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት ተመርጠው ምርጫው እንዲካሄድ ያደርጋሉ፡፡

**18.3** አስመራጭ ኮሚቴው ከሁሉ አስቀድሞ የምርጫ መመዘኛዎች በጉባዔው እንዲወሰኑ አድርጎ ምርጫውን ያስፈጽማል፡፡

**18.4** ጠቅላላ ጉባዔው የአገልግሎት ዘመናቸውን ያጠናቀቁ ወይም የተሻሩ የቀድሞ የአመራር አባላትን በክብር ያሰናብታል፡፡

**18.5** የጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔዎች በድምፅ ብልጫ ያልፋሉ፣ ድምፁ እኩል ሲሆን ሰብሳቢው ወሳኝ ድምፅ ይኖረዋል፡፡

**18.6** የማኅበሩ የስብሰባ ሥነ-ሥርዓት በማናቸውም ጊዜ ቢሆን የዲሞክራሲ መርሆዎችን የተከተለ መሆን አለበት፡፡

18.7 የአስመራጭ ኮሚቴ አባላት እራሳቸውን ለኮሚቴ ምርጫ በዕጩነት ማቅረብ አይችሉም፤ ሆኖም ግን የጠቅላላ ጉባዔው ካመነበት ከአስመራጭ ኮሚቴነት በማንሳት በእጩነት ሊያቀርባቸው ይችላል፡፡

18.8 አስመራጭ ኮሚቴው አዲሶቹ ተመራጮች 30 ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ ሥራቸውን ተረክበው እንዲሰሩ የማድረግ ኃላፊነት አለበት፡፡ የፅሁፍ ሪፖርት በአንድ ሳምንት ውስጥ ለፅ/ቤቱ ገቢ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ይህንንም የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ም/ሰብሳቢ እና ፀሃፊ በአግባቡ መፃፉን ያረጋግጣሉ፡፡

18.9 ቀድሞ ተመራጮች በምርጫ ከተሰናበቱበት ዕለት ጀምሮ ከጠቅላላ ጉባዔ ውሳኔ ውጪ ከርክክብ በስተቀር ሥራውን ማንቀሳቀስ አይችሉም፡፡ይሕንንም የጠቅላላ ጉባኤው ሰብሳቢ፣ ም/ሰብሳቢ እና ፀሃፊ በጋራ የሚያስፈፅሙት ይሆናል፡፡

18.10 በጠቅላላ ጉባዔው አጀንዳነት ቀርበው ነገር ግን ያልፀደቁና ያልሰፈሩ ጉዳዮችን በተመለከተ የተሰጡ ውሳኔዎች ተፈፃሚነት አይኖራቸውም፡፡

18.11 **በጠቅላላ ጉባኤው ላይ ላልተካፈሉ** አባል ተቋማት **የውሳኔዎች ቅጅ □እንዲደርሳቸው ይ□ረፉል**፡፡

## አንቀጽ አስራ ዘጠኝ

## የሥራ አመራር ቦርድ ሥልጣንና ተግባራት

19.1 የሥራ አመራር ቦርድ በጠቅላላ ጉባዔው የሚቋቋምና ተጠሪነቱም ለዚሁ አካል ሆኖ የማኅበሩን የዕለት ተዕለት ሥራ ያከናውናል፡፡

19.2 የሥራ አመራር ቦርድ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

ሀ. የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ ክንውን ሪፖርት በጀት ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡

ለ. የማኅበሩን ዓመታዊ የሥራ መርሀ ግብርና የረዥም ጊዜ እቅድ አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው አቅርቦ እንዲፀድቅ ያደርጋል፡፡

ሐ. የማኅበሩን ዓላማዎች ለማስፈፀም የገቢ ምንጮችን የገንዘብ፣ የጉልበት ወይም የማቴሪያል ድጋፍ የሚገኝበትን ዘዴ ያፈላልጋል፡፡

መ. የማኅበሩን ፖሊሲ እና እቅድ ወዘተቷ በማመንጨት ለ**ጠቅላላ ጉባኤ** ያቀርባል፡፡

ሠ. ሠራተኞች የሚቀጠሩበትንና የሚተዳደሩበትን ደንብ ያወጣል፣ ይቀጥራል፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ስንብት፣ ደመወዝ፣አበል እና ሌሎች ጥቅማጥቅሞችን ይወስናል፡፡

ረ. በጠቅላላ ጉባዔው የሚተላለፉ ውሳኔዎች በተግባር ላይ እንዲውሉ ያደርጋል፡፡

ሰ. የቦርዱን የአሠራር መመሪያ ሥነ ሥርዓት ያወጣል፡፡

ሸ. እንደ አስፈላጊነቱ **ቅርንጫፍ ፅ/ቤቶችን ያቋቁማል፤ በፅ/ቤቶቹም የስራ ውክልና ይሰጣል** እንደ ሁኔታው እየታየ ፅ/ቤቶቹን ይዘጋል ውክልናውንም ማንሳት ይችላል፡፡

ቀ. ፖሊሲ፣ ስትራቴጅ፣ መመሪያ ወዘተ፲ ያወጣል፡፡ እንዳስፈላጊነቱ ለጠቅላላ ጉባዔ አቅርቦ ያጸድቃል፡፡

በ. ለማህበሩ አላማ መሳካት የሚረዱ ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ያቋቁማል፡፡ ይከታተላል፡፡

**ተ. በአባል ተቋማት መካከል የሚ**ከሰቱ አለመግባባቶች **ተመልክቶ የማግባባት ስራ ይሰራል፡፡ ውጤቱንም ለጠቅላላ ጉባኤ ሪፖርት □ቀርባል፡፡**

**ቸ. □ማህበሩ ሂሳብ □እንዲመረመር ያደርጋል፡፡**

**ነ.** በጠቅላላ ጉባዔው የተሰጡትን ሌሎች ተግባሮች ያከናውናል፡፡

**19.3 ከአባላት መ**ካከል በኢጋዥነት እና በአስረጅነት የሚጠቅሙ ሰዎችን በቦርድ ውስጥ ሊያሳትፍ ይችላል፡፡ ውክልናም ሊሰጥ ይችላል፡፡

**19.4** የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ አባል የሆነ ማንኛውም ሰው በተጨማሪ ኦዲተር ወይም የማኅበሩ ጽ/ቤት ሠራተኛ ሆኖ ሊሰራ አይችልም፡፡

**19.5** የስራ አመራር ቦርድ አባላት ስራውን ለመከታተል እና ለመቆጣጠር እንዲሁም የተጣለባቸውን ሃላፊነት እንዲወጡ የስራ ክፍፍል በራሳቸው ማድረግ ይችላሉ በዚህ ወቅት አንድ ስራ አመራር ቦርድ አባል እንደ አስፈላጊነቱ ከአንድ በላይ ውክልና ሊይዝ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ

## የሥራ አመራር ቦርድ አባላት

**20.1** የሥራ አመራር ቦርድ ሰባት አባላት ይኖሩታል፡፡

**20.2** የሥራ አመራር ቦርድ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ. ኘረዚደንት

ለ. ምክትል ኘረዚደንት

ሐ. ሌሎች አባላት ብዛት ሰባት (ጠቅላላ ዘጠኝ አባላት ይኖሩታል)

መ. የማህበሩ ስራ አስኪያጅ (ድምፅ አልባ በመሆን በፀኃፊነት የሚያገለግል)

### *20.3 ፕሬዚደንት*

በጠቅላላ ጉባዔው የሚመረጥ ሲሆን የሚከተሉትን ሥራዎች ያከናውናል፡-

ሀ. ጠቅላላ ጉባዔ የሚያቋቁመውን የሥራ አመራር ቦርድ **በሰብሳቢ**ነት ይመራል፡፡

**ለ. ቦርዱ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች □ስትራቴጂዎች፣ □ቅዶች □□ተ... ለ**ጠ**ቅላላ ጉባኤ አቅርቦ □ናትቃል፡፡**

**ሐ.** ማኅበሩን በሦስተኛ ወገኖች ዘንድ ይወክላል፡፡

**መ.** ለማኅበሩ ሥራ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎችን ይፈቅዳል፡፡

**ሠ.** በማኅበሩ ስም ደብዳቤዎችን ይፈርማል፡፡

**ረ.** የሥራ አስፈፃሚ ቦርዱን በማስፈቀድ በማኅበሩ ሥም ንብረት ለመግዛትና ለመሸጥ የሚያስችሉ

ውሎችን ይዋዋላል፡፡

**ሰ.** በጠቅላላ ጉባዔው የሚተላለፉ ውሳኔዎችን በተግባር ላይ ያውላል፡፡

**ሸ.** ሌሎች **ከ**ሥራ አመራር ቦርድ የሚሰጠውን ሥራ ያከናውናል፡፡

**ቀ.** ከማህበሩ ስራ አስኪያጅ ጋር በመሆን በጣምራ ፊርማ የማህበሩን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል

### *20.4 ምክትል ፕሬዚደንት*

ሀ**.** ፕሬዚዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ ይሰራል፡፡

ለ**.** በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ተጨማሪ ሥራዎችን ያከናውናል፡፡

ሐ**.** ፕሬዝዳንቱ በማይኖርበት ጊዜ ከስራ አስኪያጁ ጋር በመሆን በጣምራ የማህበሩን ሂሳብ ያንቀሳቅሳል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አንድ

## የሥራ አስፈፃሚ ቦርድ የስብሰባ፣ የድምፅ አሰጣጥ

## ሥነ-ሥርዓትና የአባላት የአገልግሎት ዘመን

**21.1** የቦርዱ መደበኛ ስብሰባ በሦሥት ወር አንድ ጊዜ ሆኖ አስቸኳይ ስብሰባ **በሚያስፈልግበት ጊዜ** ልዩ ስብሰባ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**21.2** አስቸኳይ ስብሰባ በፕረዚደንቱ ሊጠራ ይችላል፤ ፕረዚደንቱ **በሌሉበት በም**/ፕረዚደንቱ **ሊጠራ ይችላል**፡፡

**21.3** ከአባላቱ ውስጥ ከግማሽ በላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔው እንደተሟላ ይቆጠራል፣ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ ድጋሚ ለስብሰባ ጥሪ ይደረጋል፡፡ በድጋሚ በተደረገው ጥሪ ምልዓተ ጉባዔ ካልተሟላ በተገኙ አባላት ስብሰባ ሊካሄድ ይችላል፡፡

**21.4** ውሳኔዎች በጽምፅ ብልጫ ይተላለፋል፤ ድምፁ እኩል በሚከፈልበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱ የደገፈው ሃሳብ ይፀናል፡፡

**21.5** የቦርድ አባላት የአገልግሎት ዘመን ለሶስት ዓመት ይሆናል፡፡ ሆኖም አንድ የቦርድ አባል ከሁለት ጊዜ በላይ በተከታታይ ሊመረጥ አይችልም፡፡

**21.6** የቦርድ አባላት ያለደመወዝ ያገለግላሉ፤ ሆኖም ለማኅበሩ ሥራ ለሚያወጡት ወጪዎች ማካካሻ ይከፈላል፡፡

**21.7** ከቦርድ አባላት መካከል በተለያየ እክል ምክንያት ለያዘው የሃላፊነት ስራ ብቁ አለመሆን ወይም በሌሎች ምክንያቶች በሃላፊነት መቀጠል ባለመቻሉ ከስራ ዘመኑ ከግማሽ በታች ብቻ አገልግሎት የሚሰናበትበት ሁኔታ ቢከሰት በጠቅላላ ጉባኤ ምርጫ ወቅት በተጠባባቂነት ከተያዙት ውስጥ በቅደም ተከተል ወደ ስራ አመራር ቦርድ እንዲካተት ተደርጎ እስከ ቀጣዩ ጠቅላላ ጉባኤ ስራው እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በቀጣዩ የጠቅላላ ጉባኤ ስብሰባ ቀርቦ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

**21.8** ከቦርድ አባላት መካከል በተለያየ እክል ምክንያት የተሰናበተ የስራ አመራር ቦርድ ከስራ ዘመኑ ከግማሽ በላይ አገልግሎ ከሆነ ስራው ባሉት የስራ አመራር ቦርድ ተሸፍኖ እና ተደርቦ የስራ ዘመኑ እንዲጠናቀቅ ይደረጋል፡፡

**21.9** ፕረዚደንቱ ከሃላፊነታቸውም ሆነ ከስራ አመራር ቦርድ አባልነታቸው የሚለቁ ከሆነ የበጀት አመቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በም/ፕረዚደንቱ እንዲመራ ይደረግና የበጀት አመቱ ሲጠናቀቅ ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ውሳኔ እንዲያገኝና በምትኩ ሌላ እንዲመረጥ ይደረጋል፡፡

**21.10** ፕረዚደንቱ ሆነ ም/ፕረዚደንቱ በአንድ ወቅት ወይም በተከታተይ ከስራ አመራር ቦርድ ወይም ከአባልነት ቢለቁ ለጠቅላላ ጉባኤ አስቸኳይ የስብሰባ ጥሪ በማስተላለፍ በምትካቸው ምርጫ እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡ ሆኖም ግን የምርጫ ዘመናቸው ሊጠናቀቅ ስድስት ወር ሲቀረው ከሆነ ከቀሩት ስራ አመራር ቦርድ ውስጥ በጊዜጣዊነት በመመራረጥ መሰየም ይችላሉ፡፡

**21.11** የማህበሩ ስራ እንዳይበጣጠስና ቀጣይነት እንዲኖረው አዲስ የስራ አመራር ቦርድ ምርጫ ሲደረግ ሲመረጥ ከነባሩ አመራር የአገልግሎት ዘመናቸው ካላጠናቀቁት አባላት ውስጥ **1/3**ኛው መካተት ይኖርበታል፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሁለት

## የማህበሩ ፅ/ቤት ስራ አስኪያጅ ተግባርና ሃላፊነት

### ሀ. የማህበሩ ስራ አስኪያጅ ተግባርና ሃላፊነት

□ማህበሩ ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለቦርድ ሆኖ የሚከተሉትን ሥልጠንና ተግባሮች ይኖሩታል፡፡

22.1 ከቦርዱ ወይም ከፕሬዚደንት በሚሰጠው ውክልና መሰረት ማናቸውንም ጉዳዮች ይፈጽማል፣ ቦርዱን ወይም ፕሬዝዳንቱን አማክሮ ውክልና ይሰጣል፣ በማህበሩ ስም የደብዳቤ ልውውጦችን ያደርጋል ፡፡

22.2 በማህበሩ ስም የሚከፈተውን/ የተከፈተውን የባንክ □እና ቼክ ወይም ሐዋላ ከፕሬዝዳንቱ □□ም ከምክትል ፕሬዝዳንቱ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል ፡፡

22.3 በጠቅላላው ጉባኤና በቦርድ የሚተላለፍ □ሣኔዎችን ተግባራዊ ያደርጋል ፡፡

22.4 □ማህበሩን የየሶስት ወር እና ዓመታዊ □ሥራና የፋይናንስ ሪፖርቶች እ□□ቶ□ ለቦር□ □ቀርባል ፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

22.5 □ማህበሩን የበጀት እና የሥራ እቅድ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል ፡፡ አፈፃፀሙን ይከታተላል፡፡

22.6 በመተዳደሪያ ደንቡ መሠረት ለማ□በሩ ቋሚ □ሚገኝበት □□ □ቀ□ሳል ፡፡

22.7 ቦር□ በሚያወጣው የአስተዳደር ደንብ መሠረት በስሩ ያሉትን ሠራተኞችን □ቀዓራል፣ በቦር□ □እውቅና ያሰናብታል፣ ደመወዛቸውን እና አበላቸውን ለቦርዱ አቅርቦ ያስወስናል፡፡

22.8 በስሩ ያሉትን የሰራተኞች የሥራ ድልድልና ድርሻ በማዘጋጀት ለቦርዱ ያቀርባል፣□ናትቃል ፡፡

22.9 በስሩ □ሚቶትን ሠራተኞች በሙሉ□□ስተባብራል ፣□እየተከታተለ፤□እ□ተቆ□ቷረ የማህበሩን የዕለት ተዕለት የሥራ □እንቅስቃሴ ይመራል ፡፡

22.10 የማህበሩን ን/ቤት □ሥራ □እንቅስቃሴ በተመለከተ ሌሎች የማኔጅመንነት ውሳኔዎችን ይሰጣል ፡፡

22.11 የማህበሩ መተዳደሪያ ደንብ ወይም የጠቅላላ ጉባኤ ውሣኔን በማይቃረን ሁኔታ ከቦርዱ የሚሰጡትን ሌሎች ተግባራት ያከናውናል፡፡

22.12 በማህበሩን የስራ አመራር ቦርድ ፀሃፊ ሆኖ ያገለግላል ፡፡

22.13 የተቋማት የአባልነት ማመልከቻዎች ምርምሮ ይቀበላል ፡፡ ለቦርድ አቅርቦ ያፀድቃል ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሶስት

## የውጭ ኦዲተር ኃላፊነትና ተግባር

23.1 የውጪ ኦዲተር ተጠሪነቱ ለጠቅላላው ጉባዔ ሆኖ፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች

ይኖሩታል፡፡

ሀ. የማኅበሩን የገንዘብና የንብረት አስተዳደር ትክክለኛነት ይቆጣጠራል፣

ለ. የማኅበሩን የሥራ እንቅስቃሴ በዚህ መተዳደሪያ ደንብ መሠረት መካሄዱን ያረጋግጣል፣

ሐ. በኢትዮጵያ ተቀባይነት ባገኙ መመዘኛዎች መሠረት ዓመታዊ የኦዲት ሪፖርት አዘጋጅቶ ለጠቅላላ ጉባዔው ያቀርባል፣

## አንቀጽ ሃያ አራት

## የማኅበሩ የገቢ ምንጭ

**24.1** የማኅበሩ ዋና የገቢ ምንጭ የአባላት መዋጮ ሲሆን በጠቅላላ ጉባዔው ውሳኔ መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ዕርዳታ ሰጪዎች እና ከገቢ ማስገኛ ሥራዎች የሚገኝ ገንዘብ ወይም ንብረት በገቢ ምንጭነት ሊወሰድ ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሃያ አምስት

## የማህበሩ ቅርንጫፍ ፅ/ቤት

**25.1** የማህበሩ ዋና ፅ/ቤት መቀመጫ አዲስ አበባ ይሆናል፡፡

**25.2** ማህበሩ **በክልላዊ መንግስታት □ስጥ ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡**

**25.3 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ የሚመሠረተው ቢያንስ 5 አባል ተቋማት በሚገኙበት □ልል ውስጥ ነው፡፡**

**25.4 ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱ ሰራተኞች ብዛት□እና የስራ ድርሻ በስራ አመራር ቦርድ ይወሰናል፡፡**

**25.5 በተለያዩ ክልሎች የሚገኙ የከፍተኛ ትምህርት** እና **ቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ስልጠና ተቋማት ማህበራትን በጥናት ላይ በመመስረት □እና ህጋዊ መንገድ በመከተል ሊያቅፍ ይችላል፡፡**

## አንቀጽ ሃያ ስድስት

## የቅርንጫፍ ፅ/ቤቱ ዋና ዋና ስራዎች

**26.1 □ሥራ** አመራር **ቦርድ የሚያወጣቸውን ፖሊሲዎች ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች ያስፈጽማል፡፡**

**26.2 ጠቅላላ ጉባኤውና ቦርዱ የሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች □ስ□□ማል ፡፡**

**26.3 የክልሉን ነባራዊ ሁኔ□ በማጥናት የአሰራር ሥልት በመንደፍ** ለሐገር አቀፉ የሥራ አስፈጻሚ ቦርድ **□ቀርባል ፡፡**

**26.4** ከሐገር አቀፉ **□ሥራ** አስፈጻሚ **ቦርት የሚሠጠውን ተፊ ማሪ ሥራ ያከናውናል ፡፡**

**26.5 □ማህበሩ ንብረት በጥንቃቄ □ቷብቃል ፡፡**

**26.6** የሐገር አቀፉ **□ሥራ** አስፈጻሚ **ቦርት በሚሰጠው ውክልና መሠረት አግባብነት ያለቸውን ተግባራት ሁሉ** ያከናውናል ፡፡

**26.7 ቅርን□ አ** ፅ/ቤቶች የስራ አመራር ቦርድ በሚሰጠው ውክልናና ደረሰኝ ከአባላት አመታዊ መዋጮ ገንዘብ ሊሰበስቡ ይችላሉ፡፡

## አንቀጽ ሃያ ሰባት

## የማኅበሩን መተዳደሪያ ደንብ ስለማሻሻል

**27.1** በዚህ መተዳደሪያ ደንብ የሚቀርቡ የማሻሻያ ሀሳቦች ቢኖሩ ከጠቅላላ ጉባዔው አባላት ሶስት አራተኛ ባላነሱ አባላት ጠያቂነት በስብሰባ አጀንዳነት ይያዛል፤ ማሻሻያ ሃሳቡ **3/4** ኛ ድምፅ ሲያገኝ ደንቡ ይሻሻላል፡፡

**27.2** የዚህ መተዳደሪያ ደንብ የማሻሻያ ሀሳብ በጠቅላላ ጉባዔ መደበኛ ስብሰባ የሚወሰን ሆኖ የማሻሻያ ጥያቄው ለፕሬዚዳንቱ ወይም ለማኅበሩ ጽ/ቤት የጉባዔው ጥሪ ከመሰራጨቱ ከሰባት ቀን በፊት መቅረብ ይኖርበታል፡፡

**27.3** መተዳደሪያ ደንቡ የስራ አመራር ቦርድ መቀየር እንዳለበት ሲያምንና ለጠቅላላ ጉባኤ ቀርቦ ተፈላጊው ድምፅ ሲያገኝ ሊሻሻል ይችላል፡፡

**27.4** በመንግስት የተለያዩ የፖሊሲ እና ስትራቴጂ ለውጦች ሲኖሩ እና ይህም ከማህበሩ አካሄድ ጋር ማሻሻል ሲያስፈልገው ሊሻሻል ይችላል፡፡

**27.5** እንዲሁም ሌሎች አሳማኝ ምክንያቶች ሲኖሩ፡፡

## አንቀፅ ሃያ ስምንት

## ስለማኅበሩ መዋሃድና መለወጥ

**28.1** ማኅበሩ ወደተለያዩ ማኅበራት የሚከፋፈለው፣ ከሌላ ማኅበር ጋር የሚዋሃደው ወይም ወደ ንግድ ማህበራት ምክር ቤትአባል የሚሆነው በጠቅላላ ጉባዔው በሦሥት አራተኛ ድምፅ ሲወሰን **ብቻ** ነው፡፡

**28.2** ከማኅበሩ ጋር የሚዋሃደው ማኅበር ጋር የሚደረገውን **ለውህደት □ሚ□ረፅ ትርትር** የሚያከናውነው ኮሚቴ የጠቅላላ ጉባዔው በተከናወነበት ዕለት የነበሩትን **ፕሬዝዳንቱንና** ፀሐፊ**ውን** ማካተት ይኖርበታል፡፡

## አንቀፅ ሃያ ዘጠኝ

## ስለማኅበሩ መፍረስ

**29.1** ማኅበሩ የሚፈርሰው የጠቅላላ ጉባዔ አባላት ማኅበሩ እንዲፈርስ በ□ኛ ድምፅ ሲወስኑ ነው፡፡

**29.2** ጠቅላላ ጉባዔው ማኅበሩን ለማፍረስ ከወሰነበት ቀን አንስቶ ስድስት ወራት ሳያልፍ የማኅበሩ ቦርድ የንብረት ቆጠራ **(ሽቃባስቃቋቂቄሸ)** አሰርቶ ካፀደቀ በኋላ በፕሬዚዳንቱ አማካኝነት ከማፍረስ ውሳኔው ጋር በማያያዝ በአዋጅ ስልጣን ለተሰጠው ለኢፌድሪ ንግድ ሚንስቴር የንግድ ዘርፍ ማህበራት ዳይሬክቶሬት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

**29.3** ጠቅላላ ጉባዔው ማኅበሩን ለማፍረስ በወሰደው ውሳኔ ላይ የማኅበሩን ንብረት ሊረከብ ይገባዋል የሚለውን ድርጅት ወይም ማኅበር ወይም የመንግሥት አካል ሊያመለክት ይችላል፡፡

## አንቀጽ ሰላሳ

## የመተዳደሪያ ደንብ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ የመተዳደሪያ ደንብ በጠቅላላ ጉባኤ ውሳኔ መሰረት ከፀደቀበት ቀን ከሚያዝያ **5/2011** ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡